# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 157 ግንቦት 11 2003 ገጽ 1

**በስህተትም ይሁን በሌላ ምክንያት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በህዝብ ጫንቃ ላይ ተንሰራፍቶ ከሚገኘው አጸያፊ ሥርዓት ጋር በመወገን በወገናቸው ላይ የስቃይ በትር የሚያሳርፉ አካላትና ኃይሎች በሙሉ ቀኑ ሳይጨልምባቸው ከህዝብና ከመጪው ብሩህ ዘመን ጎን እንዲሰለፉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

# ግንቦት 7 ሲዘከር

ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ - ግንቦት 7 2003 ዓ.ም

ዛሬ ግንቦት 7 2003 ዓ.ም. ነው። ይህ ቀን ለኢትዮጵያዊያን ያለው ትርጉም ከፍተኛ ነው።

ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ የነበረው ተስፋና የልበ-ሙሉነት ስሜት የምናስታውሰው ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በላዩ ላይ የተጫነበትን አገዛዝ በምርጫ ካርዱ አባሮ ይበጁኛል ያላቸውን ለመምረጥ ያለውን ጉጉት እና ችሎታ ለመላው ዓለም ያረጋገጠበት ቀን ነው - ግንቦት 7 ቀን 1997። በዚያ ቀን በተደረገው ምርጫ እና ድምጽ በአግባቡ በተቆጠረበት ጣቢያ ሁሉ የመለስ ዜናዊ ድርጅት ድርሻ ከአስር በመቶ ያነሰ ነበር።

በእለቱ በህዝቡ ልብ ውስጥ ውስጥ የነበረው የአንድነት፣ የመቻቻል፣ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ስሜቶችም ፈጽሞ የሚዘነጉ አይደሉም። ሆኖም የአዲስ አበባው ውጤት እንደታወቀ ከአዲስ አበባ ውጭ የነበረው ድምጽ ተዘረፈ። ገለልተኛ ነፃ የሆነ የምርጫ ቦርድ፣ የጦር ሠራዊት፣ የሚዲያ እና የፍትህ ተቋማት በሌሉበት በህዝብ ድምጽ የተባረረው መለስ ዜናዊ በአግዓዚ ሠራዊት ድጋፍ ሥልጣን እንደያዘ ቆየ። ያ ሁሉ ተስፋ በጉልበት ተደፈጠጠ። ምርጫ 97ን ተከትለው የመጡ የአፈና እርምጃዎች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫዎች ለማድረግ አንዳችም ፍላጎት እንደሌለው፤ በየጊዜው የሚደረጉ ምርጫዎችን የሚፈልጋቸው ለአገዛዙ ህጋዊ እውቅና ለመስጠት ብቻ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ አሳዩ።

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በጉልበት የተነጠቀውን መብት ማስመለስን ዓላማው ያደረገ፤ በኢትዮጵያ የፓለቲካ ታሪክ ውስጥ በዚህ የፓለቲካ ዓላማው ልዩ የሆነ ንቅናቄ ተወለደ። ንቅናቄው ግንቦት 7 1997ን ለመዘከር ሲልም ራሱን "ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ" ሲል ሰየመ።

ግንቦት 7 ቀን 1997 በኢትዮጵያ የነበረው ተስፋ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እስትንፋስ ነው። ዓላማውም ያንን ተስፋ ህያው ማድረግ ነው። ኢትዮጵያዊያን ተዓማኒነት ባለው ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መንግሥታቸውን መሾም እስከሚችሉ ድረስ የግንቦት 7 ትግል ይቀጥላል።

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ኢትዮጵያዊያን የሚደርስብን የሙብት ረገጣ በእለት ወደእለት እየከፋ መጥቶ ዛሬ የከፋቱ መጠን ልክ አጥቷል። የህዝባችን የኑሮ ሁኔታም በከፍተኛ ፍጥነት እያሽቆለቆለ ነው። ሁኔታዎች በአንክሮ ያስተዋለ ሁኔታ አገራችን ከግንቦት 7 ሁለ-ገብ የትግል ስልት አንዱ ለሆነው ለህዝባዊ እምቢተኝነተኝነት እየተዘጋጀች እንደሆነ ይገነዘባል። እየመጣ ያለውን ህዝባዊ እምቢተኝነትን በድል ለማጠናቀቅ ደግሞ ሁለ-ገብ ዝግጅት ያስፈልጋል፤ ለዚህም ድርጅታችን የሚያስፈልገው እያደረገ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!**

## ህዝባችን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በነጻ ምርጫ አስተዳዳሪዎቹን የመረጠበት የግንቦት7 1997 ስድስተኛው አመት ታስቦ ዋለ

የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለምንም ተጽዕኖና ግፊት በነቂስ 'ሆ' ብሎ ወጥቶ ሊያስተዳድሩኝ ይገባል ያላቸውን መሪዎቹን በምርጫ ሳጥን የመረጠበት ታሪካዊው የግንቦት 7 ቀን ስድስተኛ አመት ባለፈዉ እሁድ ግንቦት 7 ቀን 2003 ዓም ታስቦ መዋሉን የግንቦት 7 የህዝብ ግንኙነት ክፍል አስታወቀ። ይህንን ታሪካዊ ቀን አስመልክቶ ግንቦት ሰባት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች መግለጫ አውጥቷል።

ህዝብን በምርጫዉ ሳይሆን በጠመንጃ ኃይል ለመግዛት ተማምለዉ አዲስ አበባ የገቡት መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ በግንቦቱ ምርጫ ማግስት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች የምርጫ ኮሮጆ መስረቅ ብቻ ሳይሆን "የህዝብ ድምፅ ይከበር" ብሎ የወጣውን ፍትህ ፈላጊ ዜጋ በአጋዚ ጦር በመጨፍጨፍ እነሱ በህይወት እስካሉ ድረስ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ኢትዮጵያ ወስጥ እንደማይካሄድ በተግባር አረጋግጠዋል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምርጫ 97 ከደረሰበት ሽንፈት ባገኘው ትምህርት ህዝብ በነጻነት እንዳይደራጅ፤ ሃሳቡን እንዳይገልጽ፤ እንዳይሰበሰብና ምንም አይነት **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## በአዲስ አበባ የታክሲ ሾፌሮች አደሙ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ በታክሲ እጦት እየታመሰ ነው

የአዲስ አበባ ከተማ ታክሲ ሾፌሮች ባለፈዉ ሰኞ የስራ ማቆም አድማ በመጀመራቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪና በስራና በተለያዩ ምክንያቶች ከተማዋን የሚጎበኘዉ ህዝብ ከፍተኛ የመጓጓዣ ችግር እንደገጠመዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ። እንደዘጋቢያችን አባባል የዘረኛው አገዛዝ የጸጥታ ኃይሎች የታክሲ ሾፌሮች አድማዉን አቁመዉ ስራ እንዲጀምሩ ከማስገደዳቸዉ ባሻገር አንዳንዶችን ከማሰገደድ አልፈዉ ያስሩ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በትናንትናው እለት ባሰራጨው ዜና "ተነስ ምን ትጠብቃለህ? " የሚል ወረቀት ሲበተን እንደነበርና በአዲስ አበባ ከተማም ከፍተኛ ውጥረት ይታይ እንደነበር ከፍጠኛ ቁጥር ያላቸዉ የታክሲ አሽከርካሪዎች ለኢሳት ዘጋቢ መግለጻቸውን አስታዉቋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ተማሪዎች ለአባይ ግድብ ገንዘብ ካልከፈላችሁ ሞዴል ፈተና አትፈተኑም ተባሉ

በሰሜን ሸዋ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአባይ ግድብ ማሰሪያ የሚሆን ቦንድ ካልገዛችሁ ወይም ገንዘብ ካላዋጣችሁ ሞዴል ፈተና አትፈተኑም መባላቸውንና በዚህም ሳቢያ ታግተው መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ። በዘገባዉ መሰረት ከትናንት በስቲያ ተማሪዎቹ የ8ኛ ክፍልን ሞዴል ፈተና ለመውሰድ ከመቀመጣቸዉ በፊት "ለህዳሴዉ ግድብ" ማሰሪያ የሚሆን ቦንድ ግዙ ተብለዉ ሲጠየቁ "እኛ ገንዘብ የለንም ወላጆቻችንም ገንዘብ የለንም ብለውናል" ብለዉ ሲመልሱ ፈተና አትፈተኑም በመባላቸዉ በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መሃል ትልቅ ውዝግብ ተፈጥሮ እንደነበር ከአካባቢዉ የደረሰን ዜና ያመለክታል።

በሌላ በኩል ደግሞ እንደተማሪዎቹ ሁሉ ቦንድ ካልገዛችሁ ተብለዉ የተጠየቁት መምህራን በአገሪቱ ባለው የኑሮ ውድነት ምክንያት ገንዘብ ለማዋጣት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ቢገልጹም የዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎች አሻፈረን በማለት የማስገደድ ስራቸውን መቀጠላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር በሚል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የለቀቀው የአባይ ግድብ ነጠላ ዜማ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን እያስመረረ የሚገኝ ሲሆን፣ የአገዛዙ ቁንጮ የሆነዉ መለስ ዜናዊ ከግብጽ መንግስት ጋር ባደረገው ስምምነት የግድብ ስራው ግንባታ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ማድረጉን መግለጻችን አይዘነጋም።

## ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን እስከ ግንቦት መጨረሻ ድረስ እንዲያድሱ ታዘዙ፣ ከፈቃዱ ጋር ተያይዞ የመጣው ነገር ነጋዴዎችን እየጎዳ መሆኑ ተዘገበ

በቅርቡ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ባወጣው ዘገባ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ድረስ እንዲያድሱ በዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ነጋዴዎቹ እንደሚሉት አንድ ነጋዴ ፈቃዱን ከማሳደሱ በፊት ባለዉ ካፒታል ልክ ጥሬ ገንዘብ ባንክ እንዲያስገባ የሚገደድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኢሳት ከዚህ ጋር አያይዞ እንደዘገበዉ ነጋዴው ካፒታሉን በጥሬ ገንዘብ ካስቀመጠበት ባንክ ማስረጃ በመያዝ ማስረጃዉን፤ የንግድ ድርጅቱን ካርታና የባለቤትነት ማስረጃ ወረቀት በመያዝ ወደ ንግድ ፈቃድ ጽ/ቤት ካልሄደ የንግድ ፈቃዱ እንደማይታደስ ለማወቅ ተችሏል።

በንግድ ፈቃድ ማሳደሱ ዉጣ ዉረድ ያማረሩትን ነጋዴዎች ጠጋ ብለዉ ያናገሩት የኢሳት ዘጋቢዎች እንደገለጹት ችግሩ ያለው አንድም በአንድ ጊዜ ባንክ ውስጥ የሚቀመጥ ገንዘብ አፈላልጎ ማግኘት አለመቻሉ ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ ቤታቸውን ለንግድ ቤቶች ያከራዩ ሰዎች የቤት ካርታቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው ብለዋል። እነዚህን ሁለት ግዴታዎች ማሟላት ያልቻሉ ነጋዴዎች የንግድ ፈቃዳቸውን እንዲመልሱ የሚገደዱ ከመሆኑም ባሻገር ፈቃዳቸውን ሲመልሱ የ"ፈቃድ መመለሻ" ክፍያ ተገድደዉ እንደሚከፍሉ ተያይዞ የደረሰው ዘገባ አሳይቱአል። በዚህም የተነሳ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የንግድ እንቅስቃሴ ፈጽሞ እንዲሞት እየተደረገ መሆኑን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ዘግቧል።

በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነትና የዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ማለቂያ የሌለው ግፍ ያንገሸገሸው ህዝብ አመጽ ያስነሳብኛል በሚል እንቅልፍ አጥቶ የሚያድረው አገዛዝ የገበያ ዋጋን አረጋጋለሁ በሚል የተለያዩ ግብታዊ ርምጃዎችን ቢወስድም በኢትዮጵያ ውስጥ የእቃዎች መጥፋትና ይህንን ተከትሎ ዘረኛው አገዛዝ ችግሩን ለመፍታት የሚወስደው የተዘበራረቀና የተምታታ እርምጃ ህዝቡን የለውጥ ያለህ እያሰኘዉ መሆኑ በተደጋጋሚ ሲዘገብ ቆይቷል።

## ከደቡብ ክልል አዋሳ ከተማ ለተቃውሞ ወደ አዲስ አበባ የተንቀሳቀሱ 200 ምእመናን ታገቱ

ከደቡብ ክልል ርዕሰ ከተማ ከአዋሳ ቅሬታቸውን ለማሰማት ወደ አዲስ አበባ ያቀኑ የአዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አገልጋዮችና ምዕመናን ከአዲስ አበባ ሃያ ኪሎሜትር ርቀት ወደምትገኘው ዱከም ከተማ ሲደርሱ በፖሊስ መታገታቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

በዘረኛዉ አገዛዝ የታገቱት እነዚህ ምእመናን ወደ አዲስ አበባ የተጓዙት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እየተፈጸመ ያለውን በደል በተለይም መለስ ዜናዊ የቤተክርስቲያኗ ፓትሪያርክ አድርጎ የሾማቸው አባ ጳውሎስ *የሚፈጸሟቸዉን ማለቂያ የሌላቸው ጥፋቶች ለመቃወም እንደነበር ታውቋል። የምእመናኑ ጥያቄ ከላይ የተገለጸው ሆኖ ሳለ ወያኔ የግሉን ሜዲያ ለመቆጣጠር ባወጣዉ እቅድ መሰረት* ከአገዛዙ ሹመኝነት ወደ ጋዜጣ አሳታሚነት ያዛወረው የአማረ አረጋዊ ንብረት የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ግን ምእመናኑ ወደ አዲስ አበባ ያቀኑት በቅርቡ የደቡብ ክልል ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆነው በፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት የተሾሙትን ግለሰብ ለመቃወም ሲሉ ነው በማለት የአገዛዙን ነዉር የሚሸፍን የተሳሳተ ዘገባ ድህረ ገጹ ላይ አስፍሯል፡፡

ምእመናኑ ለምን ዱከም ከተማ ላይ እንደታገቱና አገዛዙ ስለ እገታው ምን ምክንያት እንደሰጠ ለማወቅ ዘጋቢያችን በስልክ ያናገራቸው አንድ ምዕመን እንደገለጹት፤ የተሰጣቸዉ ምክንያት "ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ክልክል ነው " የሚል እንደሆነና ምንም አይነት መፈክር ሳናሰማ በሰላም አፋችንን ዘግተን ከምንጓዝበት አዉቶቡስ ካወረዱን ቦኋላ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ አይቻልም ማለታቸዉ ምን እንደሆነ አልገባኝም ማለታቸውን ገልጿል።

ከዕለት ወደ ዕለት እየከፋ በመጣው ኑሮ ውድነት ህይወቱን ማቆየት የተሳነው ሰፊው የአገራችን ህዝብ የደረሰበት ብሶት ደረጃ ለሰው ልጅ መሸከም ከሚችለው በላይ እየሆነ መምጣቱን በመረጃ ሠራተኞቹ አማካይነት ያረጋገጠው የመለስ ቡድን ባልተጠበቀ ቀንና ሰአት ሊፈነዳ ይችላል ብሎ የሚሰጋውን ህዝባዊ አመጽ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

# በግንቦት 1997 ካጣነው በላይ ማግኛችን ደርሷል!

በያዝነው ሳምንት የግንቦት 7 1997 ዓ.ም. ምርጫን ስድስተኛ ዓመትና የንቅናቄዓችንን ሶስተኛ የምሥረታ ዓመትን ዘከርን። ከግንቦት 7 1997 ዓ.ም. ወዲህ ስድስት የቁጭት ዓመታትን አክብረናል። ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱ ዓመታት ያለፉት ግን ካጣናቸው መልካም ነገሮች በላይ የማስመለስ እልህ በቁጭታችን ላይ ጨምረንበት ነው። ከግንቦት 7 2000 ዓ.ም. ወዲህ በ1997 ካጣነው በላይ በትግላችን እናመጣለን በሚል ተስፋ ተሞልተናል።

የዘንድሮውን ግንቦት 7 የምናስታውሰው ዓለምን ያንቀጠቀጡ የፀረ- አምባገነን ህዝባዊ እምቢተኛነት ትግሎች በሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛው ምሥራቅ በሚንቦገቦጉበት፤ ከሰሃራ በታች ወደአሉ የአፍሪካ ሃገሮችች ዘልቆ የዩጋንዳን በር እያንኳኳ ባለበት እና ወደ አገራችን ኢትዮጵያም እንደሚዘልቅ ምልክቶች እየታዩበት ባለበት ወቅት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ የሚገኝበት አሰቃቂ ሁኔታ በቅርቡ የህዝብ አመጽ ከተቀሰቀሰባቸው ሀገር ህዝቦች ሁኔታ የከፋ ነው ። ህዝባዊ መነሳሳትን በኢትዮጵያ አይቀሬ የሚያደርገው ይህ ህዝብ ግፈኛ አገዛዞችን በመቃወም ለነፃነቱና ለመብቱ ለመሰዋት ወደ ኋላ የማይል፣ ለዚህም መነሳሳት መሰረት የሚሆን የራሱ የሆነ በቂ የታሪክ ቅርስ ያለው መሆኑ ነው።

በጭቆና የሚኖሩ ህዝቦች የግፍ በትር መፈጸሚያ ጡንቻዎቻቸውን ያፈረጠሙ መንግሥታዊ ሥርዓቶችን የማይፈሩበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ገሃድ ሆኗል። አፋኝ ሥርዓቶች ህዝብን ለለውጥና ለተቃውሞ እንዲነሳ ማድረግ የሚችሉ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ማዳከማቸው የህዝብ የነፃነት ፍላጎትን እንደማይገታ ከቱኒዝያ የተነሳው ህዝባዊ ማእበል ማስረጃ ሆኗል። መሪ በሌለበት ወይም በተዳከመበት ሁኔታ ሳይቀር ህዝብ በነፃነት ጥማት ተቃጥሎ፣ በራሱ እልህና የመከራ ሸክም ተገፍቶ ያለመሪ ድርጅትም ቢሆን ህዝባዊ የለውጥ እንቀስቃሴ መቀስቀስ እንደሚችል ገሃድ ሆኗል።

ይህ እውነታ በግንቦት7 1997 የህዝብን ድምጽ ሰርቆ፤ አናሰርቅም ያሉትን ገድሎ፣ አስሮና አሳዶ ስልጣኔን ለልጆቼ አወረሳለሁ በሚል እብሪት ተንሰራፍቶ በተቀመጠው በመለስ ዜናዊ ቤት ሽብር ለቋል። የመለስ ዜናዊ ፍርሃት መቶ በመቶ በሆነ ድምጽ ተመረጥኩ ባለበት ከተማ ውስጥ "በፈቃዱ ሊደግፈኝ ወጣ" ላለው ህዝብ ጥይት በማይበሳው መስተዋት ውስጥ ተደብቆ ንግግር በማድረጉ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። የቤተ መንግስቱን ጥበቃ ከመቼውም በላይ ማጠናከሩም አይደለም። ከተማውን በወታደርና በደህንነት ሰዎቹ ማጨናነቁ ብቻም አይደለም።

የመለስ ዜና ፍርሃት ልጓም ከማያቀው አፉ በሚፈልቀው ቅጣ ያጣ መቀባጠር እየተገለጠ ነው።

"በአምስት ዓመታት ውስጥ ሁላችሁም ዲታዎች እናደርጋለን"፤ "ኤርትራን እንወራለን"፤ "አባይን እንገነባለን" የሚሉ የማደናገሪያ ቱልቱላዎችና ድንፋታዎች አምባገነኑ እራሱ በማይቀረው ህዝባዊ አመጽ መርበትበት መጀመሩን የሚያሳዩ ናቸው። ጉልበት፣ ማጭበርበር፣ ድንፋታና ምልጃ ቤን ዓሊንና ሙባረክን እንዳላዳናቸው ሁሉ መለስም የፈለገውን እኩይና አሳዛኝ ድራማ ቢስራ ሊድን ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

የግንቦት7 1997 ምርጫ ሰጥቶት የነበረውን በክብርና በሞገስ ሥልጣን የመልቀቅ ታላቅ ታሪካዊ እድል ላይ የእብሪት ትፋቱን ተፍቶ ለዘላለም እገዛለሁ በማለት ታብዮ የነበረው መለስ ዜናዊ አይዋረዱ ውርድት ተዋርዶ ስልጣን የሚለቅበት፤ ለፈጸመው ወንጀል እና ለዘረፈው ሃብት ተጠያቂ ከሚሆንበት የታሪክ ደጃፍ ላይ ቆመን ነው የዘንድሮን ግንቦት7 የዘከርነው።

ግንቦት7 ንቅናቄ የተመሰረተበትን ሶስተኛ አመት በሚያከብርበት በዚህ የግንቦት ወር የሃገራችን ህዝብ አመጽ እያስገመገመ ነው። ንቅናቄያችን የማይቀረውን ህዝባዊ የለውጥ አመጽ እንቅስቃሴ ለመደገፍ ቆርጦ መነሳቱን ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ማናቸውም ድርጅቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለመመስረት፣ በጋራ በመስራትና ህዝብን ለመታደግ ዝግጁ መሆኑን አሁንም እንደ ትናንንቱ የማይናወጥ አቋሙ መሆኑን ግልጽ ያደረጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የግንቦት 7 ንቅናቄ በኢትዮጵያ ወስጥ የሚቀሰቀሰውን ህዘባዊ የነፃነት፣ የፍትህና የእኩልነት አመጽ አቅጣጫውን ለማሳትና በስልጣን ለመሰንበት የመለስ ዜናዊና የጥቂት ባልደረቦቹ ግፈኛ አገዛዝ ህዝብን በዘርና በሃይማኖት ልዩነት ለማፋጀት የሚሸርቡትን ደባ ለማክሸፍ ይሰራል። ህዝብ ከዚህ በፊት የከፈለውና ወደፊትም የሚከፍለው መስዋእትነት የሌላ አምባገነናዊና ግፈኛ ሥርዓት መቋቋሚያ እንዳይሆን ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ተግባር በተናጠል ይሁን ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመፈጸም ዝግጁ ነው።

ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሁሉም የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ መቀሰቀሱ ከማይቀረው ህዝባዊ እምቢተኛነት ጎን እንዲቆሙ፤ በጋራም ተባብረን ህዝብን እንድንደግፍ ግንቦት 7 ንቅናቄ ጥሪ ያቀረባል። በጋራ በመቆም ከወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ውጭ ሌላ የነጻነት የዲሞክራሲ አማራጭ እንዳለ ለህዝብ ሆነ ይህንን መስማት ለሚፈልጉ የህዝብ ወዳጆች እናሳውቅ እንላለን።

በስህተትም ይሁን በሌላ ምክንያት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በህዝብ ጫንቃ ላይ ተንሰራፍቶ ከሚገኘው አጸያፊ ሥርዓት ጋር በመወገን በወገናቸው ላይ የስቃይ በትር የሚያሳርፉ አካላትና ኃይሎች በሙሉ ቀኑ ሳይጨልምባቸው ከህዝብና ከመጪው ብሩህ ዘመን ጎን እንዲሰለፉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

## ወያኔ ዜጎችን ከመኖሪያ ቄያቸው ማፈናቀሉን ቀጥሎበታል። የፍል ውሃ አካባቢ ተፈናቃዮች የሚኖሩባቸውን ቤቶች ሊነጠቁ ነው

የዛሬ ሃያ አመት ከፍል ዉሃ አካባቢ ተፈናቅለዉ በምትኩ ሲኤምሲ አካባቢ ቦታ ተሰጥቷቸዉ ይኖሩ የነበሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ቦታችንን ሊነጥቀን የአንድ ሳምንት የግዜ ገደብ ሰጥን ሲሉ ምሬታቸዉን መግለጻቸዉን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ። እነዚህ በደል ተፈፀሙብን የሚሉ የከተማዋ ነዋሪዎች የዘረኛውና አገዛዝ ቁንጮ ለሆነው ለመለስ ዜናዊ ችግራቸውን አስመልክቶ በፖስታ ቤት በሪኮማንዴ ደብዳቤ ቢያስገቡም ምላሽ አለማግኘታቸውን ለኢሳት መግለጫ አክሎ ገልጿል።

ባለፈው ዓርብ ሚያዚያ 28 ቀን 2003 ዓ.ም፣ የቀበሌዉ ነዋሪዎች በአንድ ሳምንት ግዜ ዉስጥ ወደ ቀበሌዉ ጽህፈት ቤት ሄደዉ ካልተመዘገቡ ቤቱን ተነጥቀዉ እርምጃ እንደሚወስድባቸው አገዛዙ በተከታታይ እንዳስጠነቀቃቸዉ ኢሳት ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ዘግቧል።

ኢሳት አያይዞ ባወጣው በዚሁ ዘገባው እንደዚህ አይነቱ የቦታ ነጠቃና ማስጠንቀቂያ የደረሰባቸዉ ሰዎች ከየአካባቢዉ ተሰባስበዉ በመምከር ከአገዛዙ ጋር ለመደራደር እንዲችሉ የስብሰባ ፈቃድ ሲጠይቁ ፖሊስ ጥያቄያቸዉን ዉድቅ ከማድረጉም በላይ እናንተ የአድማ አስተባባሪዎች ናችሁ በማለት ቀደም ሲል የተመሠረተውን የነዋሪዎች ኮሚቴ ጠርቶ በማስፈራራት እንዳይሰባሰቡ ከልክሎ እንዳስጠነቀቃቸው በተጨማሪ ተገልጿል፡፡

በ1984 ዓ.ም የሽግግሩ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር በነበረው በታምራት ላይኔ ውሣኔ ከፍል ውሃ አካባቢ በልማት ስም የተፈናቀሉት አባወራዎች 552 ሲሆኑ በአማካይ በእያንዳንዱ አባወራ ቤተሰብ ውስጥ አምስት አባላት እንደነበሩ ተያይዞ የደረሰው ዜና አመልክቷል፡፡

እለታዊ ኑሮዉን መግፋት አቅቶት በስቃይ አረንቋ ፍዳውን እየቆጠረ የሚገኘዉን የኢትዮጵያ ህዝብ፣ አሁንም በማሰቃየት ላይ የሚገኘው ዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተለይም ከምርጫ 97 ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማን ህዝብ በተለያዩና ማለቂያ በሌላቸው መንገዶች የበቀል ርምጃ እየወሰደ መሰንበተን በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል:;

## የተባበሩት መንግስታት ሰራተኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገደለ፣ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር በግድያው ማዘናቸውን ገለጹ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በሶማሌ ክልል አንድ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኛ የሆነ ግለሰብ ባልታወቁ ታጣቂዎች መገደደሉንና ሌላ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኛ ደግሞ የመቁሰል አደጋ የደረሰበት መሆኑን የዓለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) ባወጣው መግለጫ አስታወቀ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ጆሴቴ ሺራን የደረሰው አደጋ እጅግ ያሳዘናቸው መሆኑን በከፍተኛ ሀዘን ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የመሰለ አደጋ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲከሰት በአንድ ወር ግዜ ዉስጥ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ዘ ሱዳን ትሪቢዩን በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ ዘግቧል። ባለፈው ወር ሌላ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ከፍተኛ ረዳት የነበረው ሳንቲኖ ፒጋ አሌክስ ዋኒ በተመሳሳይ ሁኔታ ሱዳን ውስጥ መገደሉ የሚታወስ ነዉ።

ከዚህ ዜና ብዙ ሳንወጣ ባለፈዉ ሰሞን ከአዲስ አበባ በደረሰን ዜና መሰረተ የዉሸቶች ሁሉ ምንጭ የሆነዉ ዋሾዉ በረከት ስምኦን ኢትዮጵያ ውስጥ ህይወታቸውን ላጡት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኞች ሃላፊነቱን የወሰደ አካል አለመኖሩን ተናግሮ ለዚህ ጥፋት ተጠያቂ የሚሆነው የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግምባር (ኦብነግ) ነዉ ሲል የተለመደ የቅጥፈት ክሱን መሰንዘሩን ተያይዞ የወጣው ዘገባ ያመለክታል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኛ የነበረው ፋርሃን ሃሳም ከሌሎች ሶስት የስራ ባልደረቦቹ ጋር በስራ ገበታ ላይ እንዳሉ ግድያው መፈጸሙ የተገለጸ ሲሆን ከአንድ ሟችና አንድ ቁስለኛ ውጪ ሌሎች ሁለት ሰራተኞች የደረሱበት ቦታ እስካሁን አለመታወቁንና፣ በዚህም ምክንያት እነዚህ ሁለት ሰዎች ያሉበትን አካባቢ የሚያውቁ ሰዎች ሁሉ መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩ ጥሪ መደረጉም ታውቋል። የዓለም የምግብ ፕሮግራም ከ4.5 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በሶማሊ ክልል የምግብ አቅርቦት በማድረግ ላይ እንዳለ ይታወቃል።

ይህንን አሰቃቂ ግድያ በተመለከተ አስተያየት እንዲሰጡን በስልክ ያነጋገርናቸው አንድ የክልሉ ነዋሪ እንደገለጹት የወያኔ አገዛዝ በተለይም የመገናኛ ብዙሃን ነጻ መረጃዎችን ችግር ካለባቸው አካባቢዎች እንዳይዘግቡና ለዓለም ህዝብም ይፋ እንዳያደርጉ እያፈነ፣ ራሱ ወንጀል ፈጻሚ፣ ራሱ ከሳሽ በሆነበት አገር ምን ማለት እንደምችል አላውቅም ካሉ ቦኋላ ፣ ይህ የአሁኑ ግለሰብ ግድያም ቢሆን ወያኔ እያከናወነ ያለው ስልታዊ የጥፋት ርምጃ አንዱ አካል ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ገልጸዋል።

ዘረኛው አምባገነኑና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ከኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግምባር (ኦብነግ) ጋር የሰላም ድርድር አድርጊያለሁ፣ ከዚህ በኋላ የሚከሰት ችግር አይኖርም የሚል መግለጫ ባለፈው ዓመት መጨረሻ ገደማ ቢያወጣም በአካባቢው ያለው ፖለቲካዊና ወታደራዊ አለመረጋጋት ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መምጣቱን በርካቶች ይስማሙበታል።

## ከደቡብ ክልል አዋሳ ከተማ ለተቃውሞ ወደ አዲስ አበባ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ለመቆጣጠር ያስችለኛል ብሎ የሚያስበውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ደፋ ቀና እያለ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ መግለጻችን ይታወሳል። ከሰሞኑ በደረሰን ተመሳሳይ መረጃ መሠረት በፖሊስ ሠራዊት፤በመከላከያና ደህንነት ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ሰራተኖች እንደማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በአገዛዙ አፈናና በኑሮ ዉድነቱ እየተሰቃዩ ስለሆነ እንደ ሰሜን አፍሪካዉ አይነት ህዝባዊ እንቅስቃሴ ቢጀመር የህዝቡን ጎራ ይቀላቀሉ ይሆናል የሚል ስጋት የነመለስ ዜናዊን ሰፈር ከፍጣኛ ፍርሀትና መንቀጥቀጥ እንደፈጠረ ተዉቋል።

## ህዝባችን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በነጻ ምርጫ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ተቃዉሞ እንዳያደርግ ባለፉት 6 አመታት የተለያዩ አፋኝ ህጎችና ደንቦች አርቅቆ በሥራ ላይ አዉሏል። ይህ ዘረኛ አገዛዝ ሽብርተኝነትን ለመቋቋም በሚል ሽፋን አርቅቆ ስራ ላይ ያዋለዉን "የጸረ ሽብር ህግ" ከለላ በማድረግ አያሌ ዜጎችን በማሰር፤በመደብድ፤ በመግደልና ንብረታቸዉን በመዉረስ ላይ ነዉ።

ይህንን የህዝብ ሰቆቃ ለማስቆምና ወያኔ በጠመንጃ ኃይል የሰረቀውን የህዝብ ድል ለማስመለስ መጠሪያ ስሙን ከዚሁ ታሪካዊ ዕለት ጋር በማዛመድ የተመሠረተዉ የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ባለፉት 3 አመታት በአገራችን ፍትህ ፤ እኩልነትና ነጻነት የሚሰፍንበትን ሥርዓት ለማምጣት ከፍተኛ የሆነ የትግል እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ለነፃነታችን የምናደርገው ትግል እና ነፃ ሚዲያ

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በኣቶዋ ለኢሳት ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ስብሰባ ላይ የቀረበ ኣስተያየት: ኤፕሪል 27 2011 (ክፍል 1 )

ክቡራትና ክቡራን ወገኖች:: ጎረቤት ከተማ ቶሮንቶ ብዙ ጊዜ ስመጣ ስለከተማችሁ በሩቁ ከመስማት በስተቀር በቅርብ የማየት እድል ኣላገኘሁም ነበር:: ክብር ለኢሳትና ደጋፊዎቹ ይሁንና ከተማችሁን ለማየት እድል ስለሰጣችሁኝ በመጀመሪያ ኣዘጋጆቹን ለማመስገን ይፈቀድልኝ:: ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) የገቢ ማሰባሰቢያነት በተጠራው በዚህ ታላቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ። ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ መድረክ ላይ እንድናገር በመጋበዜ ደግሞ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። ባጠቃላይ ነጻ ሚዲያው ለዴሞክራሲያዊ ስርኣት ያለውን ኣስተዋጽኦ በሚመለከት ያለኝን ጥልቅ ስሜትና ከዚህም በመነሳት ለኢሳት ያለኝን ድጋፍ (ከኢሳት በፊት ደግሞ ለኢቲኤን) የሚያውቁ የኢሳት ደጋፊዎች እኔን ከኣንድ ከተማ ወደሌላው እያንቀዠቀዡኝ እስከመቼ ሊቀጥሉ እንደፈለጉ ባላውቅምና ይህም በቅርቡ ይቆማል ብዬ ተስፋ ባደርግም ለዛሬው ግን ኣቶዋ በመምጣቴ ደስተኛ መሆኔን ለመግለጽ እወዳለሁ::

በኢሳት ጉዳይ የተሰበሰብንበት አጋጣሚ ተጠቅሜ በሚዲያ አጠቃቀም ረገድ ማድረግ ይኖርብናል ብዬ ስለማስባቸው ጉዳዮች ማንሳት አግባብነት ያለው ጉዳይ ይመስለኛል። ከሁሉ አስቀድሞ ግን እኔ የሚዲያ ባለሙያ ባለመሆኔ በብዙ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ለመናገር አልችልም። ስለሆነም ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ለባለሙያዎቹ ትቼ ነፃ ሚዲያና ለነፃነታችን በምናደርገው ትግል መካከል ስላሉ ትስስሮች ያሉኝን ሃሳቦች ላጋራችሁ እፈልጋለሁ። በዛሬው ንግግሬ በተለይ ለማትኮር የምፈልገው እያስገመገመ ያለው ህዝባዊ አብዮት ውጤታማ እንዲሆን የሚድያ ሚና ምን መሆን ይኖርበታል በሚለው ጉዳይ ላይ ነው። ለንግግሬ መንደርደርደሪያነት የሚከተሉትን ሶስት አጠቃላይ እውነታዎችን ላንሳ።

1. እንደሚታወቀው የምንገኘው በኢንፎርሜሽን ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ዘመን ዓለም ወደ ትንሽ መንደርነት ተቀይራለች። አውስትራሊያ የተፈጸመው ነገር ከመቅጽፈት አሜሪካ ይሰማል። ቱኒዝያ የተፈጸመውን ጎረቤቶቿ ሊቢያና ግብጽ ብቻ ሳይሆን እሩቅ ያለችው ቻይናም የሰሙት በአንድ ጊዜ ነው። በባኮ ከሰሞኑ የተደረገው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የእለቱ ቀን ነው በኢሳት ላይ የተነገረው:: ዜናዎች ሊደበቁ አለመቻላቸው አምባገነኖችን እያስጨነቀ ያለ ነገር ነው። በቴሌቪዥን የቀጥታ ስርጭት እየታየ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ መተኮስ የበለጠ ቁጥር ያለው ሰልፈኛን የሚጠራ ነገር ነው። ባጭሩ ዛሬ አምባነኖች ካሜራን ከጠመንጃ ባላነሰ የሚፈሩበት ዘመን ነው።
2. አምባገነኖች የመረጃ ልውውጥን ለማፈን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚያፈሱ ቢሆንም ማነቆዎችንም ለማለፍ የሚረዱ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ደግሞ አሉ። ስለሆነም እንደ አገራችን ኢትዮጵያ ባሉ የቴክኖሎጂ እድገት ታንቆ በተያዘባቸው አገሮች እንኳን ሳይቀር ከድሮ ጋር ሲነፃፀር ዛሬ የተሻሉ አማራጮች አሉን። ለምሳሌ በሚገባ ከተጠቀምንበት በኪሳችን ይዘን የምንዞረውን ተንቀሳቃሽ ስልክ (አብዛኛው) መነጋገሪያ ብቻ ሳይሆን ካሜራም መቅረፀ ድምፅም ጭምር ነው።
3. በዛሬው ዘመን መረጃ ኃይል ነው። መረጃ ሃብት ነው። መረጃ እውቀት ነው። መረጃ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። በዛሬው ጊዜ በመረጃ የበላይነት ያለው አካል በሁሉም ረገድ የበላይነትን ይጨብጣል። በመረጃ የተበለጠ ደግሞ መበለጡን የሚያካክስበት ሌላ ነገር የለም። ይህ ሃቅ ከኛ በበለጠ አምባነኖች በመረዳታቸው ቴክኖሎጂ የፈጠረውን በአንፃራዊ መልኩ ርካሽና ፈጣን የሆነው የመረጃ ፍሰትን ለማወክ እና እነሱ ለሚቆጣጠሩት ፕሮፖጋንዳ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ለማድረግ ለማመን የሚያስቸግር ሃብት ያወጣሉ። እኛ ግን በእጃችን ያለውንም በሚገባ መጠቀም ገና አልቻልንም።

### የነፃነት ትግል እና ሚዲያ

በአፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ላለው ህዝባዊ አብዮት የመጀሪያውን ክብሪት የጫረው ቱኒዚያዊው ወጣት መሃመድ ቦዛዚ ነው። የመሃመድ ቦዛዚ የምሬት እርምጃ፤ ራሱን ያቃጠለበት አስፈሪ ትዕይንት፤ ሆስፒታል በቆየባቸው ጊዜዓት የነበረበት የስቃይ ሁኔታ፤ የቀብሩ ሥነሥርዓት… ወዘተ ሰዎች የቻሉት በግል ካሜራዎቻቸውና ያልቻሉት በተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸው እያነሱ ዩ ቱብ ውስጥ ጫኑት። በአጭር ጊዜ የመሃመድ ቦዛዚ ምስሎች ዩ ቱዩብን አጥለቀለቁት። እነዚህ ምስሎች ደግሞ በፌስ ቡክ አማካይነት ሚሊዮኖች እንዲያዩት ተደረገ። እናም እሳቱ ተቀጣጠለ። መሃመድ ቦዛዚ በምሬት ራሱን ለማቃጠል የመጀመሪያው ቱኒዚያዊ ሰው ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ወዲያውኑ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን በማግኘቱ ከአገሩ አልፎ ለዓለም ቤዛ ሆኗል። መሃመድ ቦዛዚ አንዳችም የሚዲያ ሽፋን ባያገኝስ ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር? ምንም። ህዝብ በፍርሃት ቆፈን ውስጥ እንዳለ መቆዘሙን ይቀጥላል። ቤን ዓሊ፣ ሙባረክ፣ ጋዳፊ፣ ዓሊ ዓብደላ ሳልህ እንዲሁም ሌሎቹ የአካባቢው አምባገነኖች ያው እንደድሮዓቸው እየተዝናኑ "ለህዝባቸው ስላስገኙት" ልማትና ዲሞክራሲ ይደሰኩሩ ነበር። እኛ ደግሞ መሃመድ ቦዛዚ የሚባል ሰው ስለመኖሩም አናውቅም ነበር። ትንሽ ኣስገራሚ የሚድያን ሀያልነትና በተራ ግለሰቦች እጅም እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚቻል ያሳይ እንደሆን ኣንድ ምሳሌ ልስጣችሁ:: በግብጽ ላይ የክፍል ወረቀቱን የጻፈው ኣሜሪካዊ ተማሪዬ እኔ "ስለ ኣፍሪካ የእድገት ችግሮች" በማስተምረው ክፍል ውስጥ ባቀረበው የክፍል ፕሬዘንቴሽን ላይ የግብጽ የእድገት ችግሮች ኣንደኛው ምክንያት የኣምባገነኖች ግብዝነት ነው ካለ በሁዋላ ይህን ለማሳየት ሆስኒ ሙባረክ ሙሉ ሱፍ ለብሶ የተነሳውን ፎቶ ካሳየን በሁዋላ ፎቶውን ቀስ እያለ እያጎላ ኣምጥቶ ሆስኒ ሙባረክ በሚለብሰው ፒንክ እስትራይፕ ሱፍ ልብሱ ላይ በስትራይፑ ላይ ያለው ነጭ መስመር በሙሉ ሆስኒ ሙባረክ የሚል የእንግሊዝኛ ጽሁፍ እንዳለበት ነበር ያሳየን:: ማለት የፈለገውን ለማለት ከዚያ በላይ ኣላስፈለገውም ነበር::

ሌላም ተመሳሳይ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ግብጽ ውስጥ ጣህሪር አደባባይ አልጀዚራ ሌሊቱን በሙሉ ካሜራ ጠምዶ ባያድር ኖሮ ያ ሁሉ ህዝብ በሰላም ያድር ነበርን? የአልጀዚራ አዘጋጅ በሙባረክ የመጨረሻው ምሽት ከጣህሪር አዳባባይ ሰልፈኞች መካከል ጥቂቶች "ካሜራችሁ ለአፍታ እንኳን ዞር ካለ ተሰምቶ የማያውቅ እልቂት ሊከተል ይችላል ስላሉን ቀጥታ ስርጭታችንን በአደባባዩ ሳናነሳ አደርን" ብሏል። የአልጀዚራ የቀጥታ ስርጭት አደባባዩ ላለ ህዝብ መከታ ሆኗል። ክስተቱ በመላው ዓለም ዓይን ውስጥ ያለ መሆኑ የሙባረክ መንግሥትም ሆነ ወታደሩ የጭፍን እርምጃ ከመውሰድ አቅቧቸዋል። ጣህሪር አደባባይ እንዲዚያ የዓለም ሁሉ ዓይን ማረፊያ ባይሆን ኖሮ የወታደሩ አንፃራዊ ቁጥብነት እንዳየነው ይሆን ነበርን?

ለቱኒያና ግብጽ ህዝባዊ አብዮቶች ስኬት ኢንተርኔት (በተለይም ፌስ ቡክ፣ ትዊተር እና ዩ ቱዩብ)፣ የኪስ ስልኮችና ሳተላይት ቴሌቪዥኖች (በተለይም አልጀዚራ) ቁልፍ አስተዋጽዖ ነበራቸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አብዮቱ መነሳቱ አይቀሬ ስለመሆኑ ባለፉት ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ በተከታታይ የተናገርኩበት ርዕስ ስለሆነ አሁን አልመለስበትም። ይልቁንስ እያስጨነቀኝ ያለው ጉዳይ "የኛ አልጀዚራ ማነው?" የሚለው ጥያቄ ነው። በቂ የሚዲያ ሽፋን ካላገኘ በኢትዮጵያ የሚቀሰቀው ህዝባዊ አብዮት ስኬታማ የመሆን እድሉ አነስተኛ ነው። ስለዚህም ነው ሁላችንም የምር ልናስብበት የሚገባ እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ብዬ የማምነው።

### እጃችን ውስጥ ምን አለን?

#### 1. ፌስ ቡክ

ኢትዮጵያ ውስጥ የከተማ ነዋሪው ህዝብ ከጠቅላላው ህዝብ ከ15% እጅግም ያልበለጠ ቢሆንም የከተማውን ነዋሪ ማስተባበር መቻል የገጠሩን ህዝብ ለማነሳሳት ያስችላል። ሆኖም ከከተማ ነዋሪውም ውስጥ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ብዛት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በመለስ ፀረ-ኢንተርኔት ፓሊሲ ምክንያት ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር አገራችን ውስጥ የፌስ ቡክ ተጠቃሚ ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው። በአንዳንድ የአፍሪቃ አገሮች የህዝባቸው 20 % በላይ የፌስ ቡክ ተጠቃሚ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን 0.3% ብቻ ነው። ይህ በራሱ የወያኔ "ፈጣን" የኢኮኖሚ እድገት አንዱ ማሳያ ነው። ሆኖም ግን በጥበብ ከተጠቀምንበት ይህ 0.3% በመቶም ቀላል ቁጥር አይደለም። በዚህ ስሌት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮያ ውስጥ 270 000 ያህል ሰዎች ፌስ ቡክ ይጠቀማሉ። በቅርቡ የተቋቋመው "የድል ቀን" የተባለው ፌስ ቡክ (በነገራችን ላይ በጣም ከጊዜው ጋር የሚሄድ ሆኖ ኣግኝቼዋለሁ) በተቋቋመ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ 10 000 ደንበኞችን በማፍራት አደራጆቹን አስደንቆ ነበር። አሁን 12 700 አካባቢ ቆሟል። ከእነዚህም ውስጥ በርከት ያሉት በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። ከ270 000 ውስጥ 10 000 ማግኘት በጣም ትንሽ ነው። ከዚህ የምንረዳው ፌስ ቡክን እንደገና ልናጠናው የሚገባ ያልተነካ ሚዲያ መሆኑ ነው።

የፊስ ቡክ አንዱ ችግን በአገዛዙ በቀላሉ ሊዘጋ የሚችል መሆኑ ነው። አሁን በተደረገው ትንሽ ሙከራም በመደናገጥ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሰርቨር ፌስ ቡክን መዝጋቱ ተነግሯል። ስለዚህ የተዘጉ ሰርቨሮችን ማለፊያ መንገዶች መፈለግ ይኖርባቸዋል። በአሁኑ ሰዓት በርካታ ፕሮክሲ ሰርቨሮች እንዳሉ ይታወቃል። ይህ የባለሙያዎች ሥራ ነውና ለእነሱ ልተወው። ለማሳሰብ የምፈልገው ግን እንዲህ ዓይነት ሥራዎችን በተደራጀ መንገድ መሥራት ያለብን መሆኑን ነው።

#### 2. ዩ ቲዩብ

በግል የምናነሳቸውን ቪዲዮዎች በዩ ቱዩብ በመጫን ወዲያውኑ ለህዝብ እይታ እንዲዳጻረስ የማድረግ ልምድ ማዳበር ይኖርብናል። የእስካሁን ልምዳችን እጅግም የሚያበረታታ ባይሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ልናዳብረው እንችላለን። በካሜራም ሆነ በተንቀሳቃሽ ስልኮች የተነሱ የቪዲዮ ምስሎች እንዴት ወደ ዩ ቲዩብ እንደሚጫኑ በቂ ማብራሪያዎች ሊሰጡ ይገባል። በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ስለእነዚህ ጉዳዮች በቂ እውቀት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል። በዚህና ተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሬድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ቢዘጋጁ፤ መመሪያዎቹም በፌስ ቡክና ከተቻለም በ ኤስ ኤም ኤስ ቢተላለፉ መልካም ነው እላለሁ።

#### 3. የኤሌክትሮኒክስ ፓስታዎች

ኢትዮጵያ ውስጥ በግምት 3 ሚሊዮን ያህል ሰው ኢሜል ይጠቀማል። ከዚህ ውስጥ ስንቱ ሰው ነው የየሳምንቱ እትሞቻችንን በኢሜሉ የሚደርሰው ብለን ብንጠይቅ በራሳችን እናፍራለን። የጅምላ ኢሚል አላላክ የራሱ የሆኑ ቴክኒካዊ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም በጥልቅ አስበንበት መፍትሄ ልናገኝለት ይገባል። ኢሜል እስካሁን በአግባቡ ያልተጠቀምንበት ሚዲያ ነው። ድርጅቶች በየጊዜው የሚያወጧቸው መግለጫዎች፤ በድረገፆች የሚወጡ ጽሁፎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኘው ወገናችን በኢሜል ሳጥኑ ውስጥ የሚገባበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል። አንድ ጽሁፍ ዌብ ሳይት ላይ ወጣ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ተነበበ ማለት እንዳልሆነ ሁሉም የሚረዳው ይመስለኛል። እንደሚታወቀው ብዙዎች የዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆኑ ዌብ ሳይቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘግተዋል። ያልተዘጉትንም ቢሆን በኢትዮጵያው ጎታታ ኢንተርኔት ከድረገጽ ላይ ማንበብ ትዕግሥት አስጨራሽ ነው። ኢሜሎችን መጠቀም አንድ አማራጭ መፍትሄ ሊሆን ይችላል።

#### 4. ቪሲዲዎች እና ዲቪዲዎች ማተም

ንግግሮችን፣ ቀስቃሽ ድራማዎችን ወይም የራድዮ ዝግጅቶችን በሲዲና ዲቪዲ ቀርፆ ኢትዮጵያ ውስጥ በድብቅ እንዲሰራጭ ማድረግ (ለምሳሌ በቅርቡ ኣቡነ መቃርዮስ ለኢሳት የሰጡት ድንቅ ቃለምልልስ) በስፋት ልንሰራው የሚገባ ተግባር ነው። በዚህ መንገድ ድምጽን፣ ምስልንና ጽሁፎችን ማስገባት ይቻላል።

#### 5. አጫጭር መልዕክቶች

በተንቀሳቃሽ ስልኮች አማካይነት የሚላኩ አጫጭር መልዕክቶች በምርጫ 97 ወቅትም ዝና ያተረፉ የቅስቀሳና የመገናኛ ዘዴዎች ነበሩ። የመለስ አገዛዝ ለዚህ እንቅስቃሴ የሰጠው ምላሽ አገልግሎቱን መዝጋት እንደነበረ የምናስታውሰው ነበር። አሁን አገዛዙ አገልግሎቱን መልሶ እስኪዘጋው ድረስ ልንጠቀምበት የሚገባ የመገናኛ አውታር ነው።

#### 6. ፓልቶኮች

ከምርጫ 97 ወዲህ በውጭ አገራት በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ተወዳጅነት ካገኙ የሚዲያ ዓይነቶች ፓልቶኮች ግንባር ቀደም ናቸው። በአግባቡ በሥራ ላይ ከዋሉ ፓልቶኮች በጣም ጠቃሚ የሆነ የሚዲያ አውታሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ከሁሉ አስቀድሞ ግን ራሳቸውን መርምረው ድክመቶቻቸውን ማስወገድና ጥንካሬዎቻቸውን ማጎልበት ይኖርባቸዋል።

"በህዝባዊው አብዮት ውስጥ የፓልቶካችን ሚና ምን መሆን ይገባዋል?" በሚል ርዕስ ተወያይተው የጋራ መግባባት ላይ ቢደርሱና ራሳቸው ቢያደራጁ ለነፃነት ትግሉ ወገንተኛ የሆኑት ፓልቶኮቻችን እጅግ ጠቃሚ የሆነ የሚዲያ አውታሮቻችን ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ ፓልቶኮች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን ህዝባችንን የሚደርሱበት መንገድ ከአሁኑ መቀየስ ይኖርባቸዋል። **(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)**

## በወያኔ አገዛዝ ዘመንና በቀደምቶቹ 2 መንግሥታት መካከል ስላለው የመሬት ፖሊሲ ልዩነት እንዲብራራለት አስተማሪውን በመጠየቁ ለእስር የበቃው ተማሪ አስቻለው ቢራቱ በከፍተኛ ስቃይ ላይ መሆኑ ተዘገበ

በቀደሙት ሁለት መንግሥታትና አሁን በስልጣን ላይ ባለው አገዛዝ የመሬት ፖሊሲ መካከል ያለው ልዩነት እንዲገለጽለት የምጣኔ ሐብት አስተማሪዉን በትምህረት ክፍለ ጊዜ የጠየቀው ተማሪ ተማሪዎችን ለአመጽ የሚያነሳሳ የፖለቲካ ጥያቄ ጠይቀሃል ተብሎ ለእስር የተዳረገው ተማሪ አስቻለው ቢራቱ በታሰረበት እስር ቤት ውስጥ ለከፍተኛ የምግብ ችግር መዳረጉን ኢሳት ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል።

በአሁኑ ሰዓት በቡታጀራ እስር ቤት ውስጥ የሚገኘው ተማሪ አስቻለው ከላይ የተገለጸውን ጥያቄ በመጠየቁ ብቻ ወንጀለኛ ተደርጎ ፍርድ ቤት ከቀረበ ቦኋላ የአንድ አመት ጽኑ አስራት እንደተፈረደበትና ወላጆቹ ውሳነውን ተቃውመዉ ይግባኝ ቢጠይቅም ፍርዱ እንጸናበት ቀደም ሲል መዘገቡ ይታወሳል።

በዘንድሮው አመት የ12ኛ ክፍል መሰናዶ ተማሪ የነበረው ተማሪ አስቻለው በሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ላይ እንደሚደረገው በሃሰት በተቀነባበሩ 7 ክሶች የተከሰሰ ሲሆን ክሶቹም ተማሪውን ለአመጽ ለማነሳሳት፤ የመማር የማስተማር ሂደቱን ለማወክ፤ የጸረ ሰላም ሃይሎች መሳሪያ በመሆን ሰላምና እድገት ለማደፍረስ ወዘተ የሚሉ በተቃዋሚዎች ላይ በተከታታይ የሚቀርቡ ተራ የዉንጀላ ክሶች ናቸዉ።

ተማሪ አስቻለው ፈጽመሀል በተባለው ጥፋት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ አመት እስራት እንዲቀጣ የወሰነበት በመሆኑ የዘንድሮውን ማትሪክ ፈተና መውሰድ እንደማይችል የታወቀ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቤተሰቦቹ ከሚገኙበት ከቡታ ጅራ ርቆ ሆሳእና ዉስጥ በሚገኘው ማረሚያ ቤት እንዲታሰር በመደረጉ ተማሪው ከፍተኛ የምግብና የአልባሳት ችግር ገጥሞት እንደነበር የሆሳእና ማረሚያ ቤት በቁጥር ደኢማ 13/1926/ 03 የጻፈው ደብዳቤ ማመልከቱን ኢሳት ዘግቧል።

ተማሪ አስቻለው በትምህርቱ ጎበዝ ከመሆኑም በላይ ለተማሪዎች ሙብት የሚሟገት በመሆኑ አብረውት የሚማሩት ተማሪዎች በጣም እንደሚወዱትና እንደሚያከብሩት ኢሳት የዘገበ ሲሆን ተማሪው በአካባቢው ያለው አስተዳዳር መበላሸት፣ መንግስት ትምህርት ቤቱን የፖለቲካ መናሀሪያ ማድረጉንና በመምህራን ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ሳይቀር አጥብቆ በመቃወም የሚታወቅ ከእድሜው በላይ በሳልና ደፋር ነው ተብሏል።

## ወያኔ ህዝባዊ አመጽ ሊቀሰቅሱብኝ ነው የሚላቸውን ማሰር ቀጥሎአል። በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በርካታ ተማሪዎች ታስረዋል

ከዛሬ ነገ መጡብኝ በሚል ፍርሀት የተዋጠዉ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ንጹህ ዜጎችን ማሰር ስልጣኑን የሚያራዝምለት ይመስል በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ የሆነ የእስር ዘመቻ መጀመሩን መድረክ የተባለው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ ከሰሞኑ ከወደ አዲስ አበባ ባሰራጨው ዜና ገለጸ። መድረክ ባሰራጨዉ በዚሁ ዜና አያይዞ እንደገለጸዉ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ስርአት በየቀኑ እየወሰደ ባለዉ የቀቢፀ ተስፋ እርምጃ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ጨምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸዉ የኦሮሞ ተወላጆች በጅምላ እየታሰሩ መሆኑን ገልጿል።

ሰዎችን በሰብእናቸዉ ሳይሆን ከተወለዱበት ብሔረሰብ አኳያ ብቻ የሚመለከተዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ እሱና ጓደኞቹ ለፈጠሩት የአንድ ጎሳ የበላይነት ስርአት አስጊ ናቸዉ ብሎ የጠረጠራቸዉን ሁሉ እስር ቤት እየወረወረ ከፍተኛ የሆነ የአካልና የህሊና ሰቆቃ እያደረሰባቸዉ መሆኑን መድረክ አክሎ ገልጿል። ከፍተኛ የመድረክ አመራር አባል የሆኑት ዶ|ር መራራ ጉዲና ይህንን አስመልክቶ ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ በሰጡት ቃለመጠይቅ "የኦነግ አባላት ናቸው" እየተባለ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የነበሩ የመመረቂያ ግዜያቸዉን በጉጉት ይጠባበቁ ብዛት ያላቸዉ የኦሮሞ ተማሪዎች እየታፈኑ ወደ እስር ቤት እንደሚወሰዱና፤ በየእስርቤቱ ከፍተኛ ድብደባና ስቆቃ ይፈጸምባቸዋል ሲሉ ዶ/ር መረራ በምሬት ተናግረዋል።

የወያኔ ስርአት ይህንን የመሰለ መጠነ ሰፊ የእስር ዘመቻ የከፈተዉ ሰሜን አፍሪካ ዉስጥ አምባገነኖችን ለብልቦ መድረሻ ያሳጣዉን የአብዮት ሰደድ እሳት ኢትዮጵያም ውስጥ ለማቀጣጠል ተግተው የሚሠሩ ሃይሎች አሉ በሚል ሰበብ ሲሆን የጥቃት ኢላማዉ በተናጠል በኦሮሞ ተወላጆች ለምን አንዳነጣጠረ ግን ለጊዜው በዉል የታወቀ ነገር የለም። ሆኖም አንዳንድ ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደሚናገሩት በኦሮሚያ ውስጥ ለረጅም ግዜ ኦነግን ትደግፉላችሁ በሚል ሰበብ ብቻ በህዝቡ ላይ የሚፈፀመዉ ሂሊናን የሚሰቀጥጥ በደል ወጣቱን ክፍል እጅግ እያስቆጣ ስለመጣ በአገራችን ውስጥ በዬትኛውም ጊዜና ቦታ ሊፈነዳ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀዉን ህዝባዊ አብዮት ኦሮሚያ ዉስጥ ሊጀምር ይችላል የሚል ስጋት ወያኔን ስላስጨነቀዉ እንደሆነ በግልፅ ይነገራል።

ፍትህ እኩልነትና ዲሞክራሲን አገራችን ዉስጥ ማስፈን የሚቻለው የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ ለራሱ የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ሲል የገነባዉን የዘር ግድግዳ አራርሶ የህብረት ትግል ሲጀምር መሆኑ የገባቸዉ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ተሰባስበዉ በጋራ መታገል መጀመራቸዉ ወያኔን ክፉኛ እንዳሰደነገጠዉ ብዙ ተአማኒነት ያላቸዉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። የኢትዮጵያዉያን ህብረት ወያኔን እርቃኑን አስቀርቶታል የሚሉ አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የወያኔ የድህንነት ሃላፊ፤ ህዝቡ በጋራ 'ሆ ' ብሎ ወደጎዳና ከወጣና የወያኔን ጥቃት ተቋቁሞ እንደ ግብፅና ቱኒዝያ ህዝብ በጽናት ከቆመ እጃቸዉ በደም ከተነከረዉ ከመለስና በረከት ስምዖን በስተቀር ሁሉም የኢህዴግ አባላት የህዝቡን ትግል ከመቀላቀል ወደኋላ እንደማይሉ በእርግጠኛነት ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊ ኦህዴድ የኦነግ ታናሽ ወንድም ነዉ በሚል ሰበብ በኦህዴድ አባላትና በኦሮሞ ህዝብ ላይ የጀመረው የእስር ዘመቻ በሰላም አገር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ወደሚገኙ የኦሮሞ ድርጅቶች ዘልቆ በመግባት ባለፈዉ ሳምንት የኤፌዴን ምክትል ዋና ጸሀፊ የሆኑት የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ መምህር አቶ ብርሀኑ እምሩን ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ዉጭ አስሮ ቃሊቲ መወርወሩን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል።

## ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዝዝ የጽጥታ ሀይሎቹ ማንኛውንም ክትትል እንዲያድርጉ አዘዘ

የግንቦት20 በአል አከባባርን ለማደናቀፍና ብሎም ህዝባዊ አመጽ ለመቀስቀስ አንዳንድ ወገኖች እያሴሩ ስለሆነ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል ሲል የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በአገሪቱ ላሉ ወረዳዎች ሁሉ ሰርኩላር ማስተላለፉን ኢሳት የተባለው የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን ዘገበ።

ኢሳት ኢትዮጵያ ዉስጥ ከተለያዩ ወረዳ ባለስልጣኖች አገኘሁት ባለው መረጃ መሠረት ወያኔ በትረ ሥልጣን የተቆጣጠረበትን 20ኛውን የግንቦት 20 በአል በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ሽር ጉዱን የተያያዘው ሲሆን ፣ በዚህ እለት ረብሻ ለማስነሳት የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች መኖራቸውን ደርሼበታለሁ በማለት በመላዉ አገሪቱ ታላቅ የጸጥታ እንቅስቃሴ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

የመለስ ዜናዊና የባለቤቱ የአዘብ መስፍን አገዛዝ በየክልሉ የሚገኙት የጸጥታ ሀይሎች ሁከትና ረብሻ እንፈጥራለን የሚሉ ሀይሎችን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ጥብቅ ትዕዛዝ ያስተላለፈ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰሜን አፍሪካ ዉስጥ አምባገነኖችን እያርበደበደ ያለዉ ህዝባዊ አብዮት ኢትዮጵያ ዉስጥ እንዳይደርስ ለመከላከል በሚል ሰበብ በርካታ ንጹሏን ዜጎችን ማዋከብና ማንገላታት ከጀመረ ሰንበት ብሏል። በተለይ ካለፈው ሁለት ወር ወዲህ በኦሮሚያና በአማራ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች የተጀመረው የዘፈቀደ ፍተሻ አገዛዙ የደረሰበትን ከፍተኛ የስነልቦና መረበሽ ከማሳየቱም ባሻገር በጸጥታ ጥበቃው ሥራ ላይ የተሰማሩት በርካታ የበታች ሠራተኞች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ አገሪቱ ዉስጥ በተንሰራፋዉ ዘረኝነትና የኑሮ ዉድነት ዘረኛነትና በኑሮ ውድነት የተንገፈገፉ በመሆናቸው ይነሳል ተብሎ የሚጠበቀውን ህዝባዊ አመጽ በቀላሉ መቀላቀል እንደሚችሉ በከፍተኛ እምነት አለ።

ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚደረሱን ዘገባዎች እንደሚያስረዱት በአንዳንድ የአገዛዙ ፖሊሶች እቃ አንጠልጥለው የሚጓዙ መንገደኖችን ሳይቀር እያስቆሙ መፈተሽ መጀመራቸውንና ይህም ወያኔ በምን አይነት ድንጋጤ ውስጥ እንደተዘፈቀ አመልካች ነው ተብሎአል።

በአሁኑ ጊዜ በመላው አገሪቱ በየቀኑ እያሻቀበ የሚሄደዉ የዕቃዎች ዋጋና አላስቆም አላስቀምጥ ያለዉ የሙብት አፈና የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ቤት ያንኳኳ በመሆኑ አመጽ መቀስቀሱ የማይቀር ሙኑንና ከተቀሰቀሰ ደግሞ ህዝቡ እንደሰሜን አፍሪካው “ሆ” ብሎ በመውጣት በሙስናና ዘረፋ የተጨማለቀውን የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ እንደሚገረስስ ብዙዎች ይስማማሉ።

## በአዲስ አበባ የታክሲ ሾፌሮች አደሙ፣ የአዲስ አበባ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

(ከገጽ 1 የዞረ)

የዘረኛው አገዛዝ ደህንነት አባላት የቆሙ ታክሲ ባለቤቶችን እየጠሩ ስራ እንዲጀምሩ ቢጠይቁም ባለንብረቶቹ እኛ የምናዉቀዉ ነገር የለም ሾፌሮችን ጠይቋቸው የሚል መልስ መስጠታቸው የታወቀ ሲሆን በዚህ የተበሳጩት የወያኔ ደህንነት አባላት አንዳንድ ሾፌሮችን መያዝና ማሰር የጀመሩ መሆናቸው ተገልጿል።

ኢሳት ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ባገኘው መረጃ መሰረት እነመለስ ዜናዊ በአዲስ አበባ ያለውን የታክሲ ትራንስፖርት እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ በወያኔ የንግድ ኩባኒያዎች ለማስያዝ ባላቸው እቅድ መሠረት የስራውን አዋጭነት ለማስጠናት ከዚህ ቀደም በተለያዩ የአረብ አገሮች የታክሲ የአሰራር ስርአት እንዳጠና ለሚነገርለት አንድ ህንዳዊ ኤክስፐርት ኮንትራት ስጥተው ያስጠኑ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የአዲስ አበባ ታክሲ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች በምርጫ97 ወቅት ቅንጅት ጠርቶት የነበረውን ህዝባዊ ሰልፍ በማስተባበር፣ነጻ የታክሲ አገልግሎት በመስጠትና፣ቅንጅትን በመደገፍ ከስራቸው ጋር ጎን ለጎን ከፍተኛ ቅስቀሳ በማካሄድ ድጋፍ ይሰጡ ስለነበር ከአሁን ቦኋላ ተመሳሳይ አጋጣሚ እንዳይፈጠር ወያኔ የከተማውን የታክሲ ንግድ ለመቆጣጠር ውሳኔ እንዳደረገ ታውቆአል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት የታክሲ ባለንብረቶችና አሽከርካሪዎች ከሰባ በመቶ በላይ የሚሆኑት የጉራጌና የኦሮሞ ተወላጆች በመሆናቸው ማንኛውም አይነት ተቃውሞ ከተነሳ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ከመደገፍና በአድማ ተሳታፊ ከመሆን ወደኋላ አይሉም ብለዉ የሚያምኑት መለስ ዜናዊ፤ የአዘብ መስፍንና በረከት ስምዖን ከዚህ ስጋት ለመዳን ብቸኛዉ አማራጭ የታክሲ ንግድን ሙሉ በሙሉ እነርሱ በሚቆጣጠሩት የኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ማስያዝ መሆኑን ይስማማሙበታል።

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ ከሱ ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲቋቋሙ እነሱን የሚመስል ተለጣፊ በማበጀት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዳቀጨጨ ሁሉ በንግዱም ክፍለ ኢኮኖሚም የተሰማራውን ህብረተሰብ ለማዳከምና ከዉድድር ዉጭ ለማድረግ በሚያደርገዉ ጥረት እሱ እራሱ በሚቆጣጠራቸው የንግድ ድርጅቶች ስም ወይም ለሱ ታማኝ የሆኑ ተለጣፊ ባለሀብቶችን በማሰማራት የአገሪቱን ሃብት በየመስኩ እየተቆጣጠረ እንደሆነ ይታወቃል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተጀመረው የታክሲዎች የሥራ ማቆም አድማ ያስደነገጠው ወያኔ ታክሲዎች በአስቸኳይ ሥራ ካልጀመሩ እርምጃ እንደሚወስድ እየዛተ እንደሚገኝ የገለጸው ዘጋቢያችን - አዲስ አበባ ውጥረት አርግዛለች መች እንደምትገለገል ግብ ለጊዜዉ ምንም የታወቀ ነገር የለም ብሏል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org